# ፊኛው ተነፈሰ

ድሮም ብለን ነበር -ያልነውም ደረሰ
የተከየው ሁሉ - ህጉ ተገሰሰ
ውርደት ተከናንቦ -ፊኛው ተነፈሰ።

በዚህ ግንቦት ምርጫ - ያልተልከሰከሰው
እንደ ኮራ ያለው - እንዳማረበት ሰው
ኢሕአፓ ብቻ ነው -ድል የተላበሰው።

ያላወቀው ይወቅ - የወያኔን ፀባይ
ባገር ስም ነጋዴው - ዐይን አውጣው አተላይ
ልፍስፍስ ቡድኖች - ተቃዋሚ ነኝ ባይ
ከሰው ኪስ መግባቱን - ያቁም ባደበባይ።

ራስን ማሞኘት - ‘ዶሮ ሲያውቅ ማታ‘
እያዩ አለማየት - ጆሮ ላይ ምኝታ
ቢልቱ ይቅርና - ይነደፍ ቁም ነገር
በተቃዋሚው ላይ - አገር ይነጋገር !!!!!!

ግንቦት 2002 ዓብረሃም በየነ

EthioLion.Com